# ለክቡር ኒልሰን ማንደላ ማስታወሻ

ከዘኢትዮጵያ

የማይሞት ሰው ሞተ ሆነና ተፈጥሮ
ሄደ ላይመለስ መልካም ሥራ አስተምሮ
በብልጠት በመላ አፍታቶ ቋጠሮ
ጥሩውን፣ መጥፎውን፣ መከራ ተድላውን
በትዕግሥት፣ በጥበብ አስማምቶ ሁሉን
ለዓለም አበርክቶ ቆራጥና ፅናት ሕያው ተግባሩን።

እማማ አፍሪካዬ በጣም አዘነች
ዋርካውን ምርጥ ልጅ ማንደላን አጣች
ለወገኑ ብሎ ሕይወት የሰጠው
ሃያ ሰባት ዓመት እስር ያልገታው
በዓላማው የፀና ሁሉንም ያየው
በድል አድራጊነት ነፃ ያወጣው
ዘለዓለም ያበራል ማንደላ ሥራው
ለትውልድ የሚታይ ምግባር ፀሐይ ጮራው።

እማማ አፍሪካዬ በጣም አዘነች
ዋርካውን ምርጥ ልጅ ማንደላን አጣች
ዘመኑ ከባድ ነው አሁን ስትለየን
በውጭ እንቬስተር ስም ወራሪ ሲይዘን
የበፊቷ አፍሪካ አንተን የወለደች
ነበረች ከአምላክ ፅንሷን ያስባረከች
ያሁኗ አፍሪካ ግን ኅጠኛ ፈጠረች
እሾህ አሚኬላ አረም አበቀለች
ምናምን ወበሎ እንክርዳድ አፈራች
ራስ ጭንላቷን በባእድ አስያዘች።

እማማ አፍሪካዬ ፍጹም ሰው፣ምርጥ ልጅሽን  አጣች
በዚህ መጥፎ ጊዜ፣ የማይሆን ሆነና ትልቅ ሰውን ሾኘች
እማማ አፍሪካዬ አምላክ ያጠንክርሽ፣
እማማ አፍሪካዬ እግዚአብሔር ይቸርሽ
ጥሩ ልጅ በማጣት ሃዘን እንዳይጐዳሽ
አምላክ፣ አምላክ ነፍስ ይማር ማንደላን በገነት ያኑር
በማንደላ አይነት እሺውን ይፍጠር
የማንደላን ፈለግ እሺውን ይፍጠር !